'አንዳችሁ ከሆዱ ውስጥ አንዳችን ነገር ያገኘ ጊዜ ከሆዱ አንዳች ነገር ወጥቷል ወይስ አልወጣም የሚለውን መለየት ካስቸገረው ድምፅ እስኪሰማ ወይም ሽታ እስኪያገኝ ድረስ (ሶላቱን አቋርጦ) ከመስጂድ አይውጣ።'

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልዕክተኛ
(የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: 'አንዳችሁ ከሆዱ ውስጥ አንዳችን ነገር ያገኘ ጊዜ ከሆዱ አንዳች ነገር ወጥቷል ወይስ አልወጣም የሚለውን መለየት ካስቸገረው ድምፅ እስኪሰማ ወይም ሽታ እስኪያገኝ ድረስ (ሶላቱን አቋርጦ) ከመስጂድ አይውጣ።'"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ሰጋጅ ከሆዱ ውስጥ አንዳች ነገር መውጣት አለመውጣቱን አስመልክቶ ከተጠራጠረ የፈስ ድምፅ በመስማት ወይም ጠረን በማሽተት ዉዱእ የሚያጠፋ ነገር መከሰቱን እርግጠኛ እስኪሆን ድረስ ዉዱእ ለመድገም ብሎ ሶላቱን አቋርጦ አይውጣ። የተረጋገጠ ነገር በጥርጣሬ አይበላሽምና። እሱ ዉዱእ እንደነበረው እርግጠኛ ነው። ዉዱእ ማጥፋቱ ግን አጠራጣሪ ነገር ነው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/65083